

49-1

# ተጠንቀቁ!
## ራስ ወዳድነት ትምክህተኛ ያደርጋል

*"…በራስ ወዳድነት ወይም "ያለ እኔ ማን አለ" በሚል ትምክህት ምንም ነገር አታድርጉ" (ፊሊጵስዩስ 2፥3)።*

*"የሚያንሸራትት መንገድ!" "አደገና ቁልቁለት!" ድልድዩ ያዳልጣል!" "መርዝ ነው!" "የሚያሰክር መጠጥ ጠጥተህ አትንዳ!" የሚሉ የማስጠንቀቂያ ምልክቶችን ማየት ዓይናችን የለመዳቸው ቢሆኑም፥ ለጌጥ የተደረጉ አይደሉም። ከአደጋ፣ ከጥፋትና እንዲሁም ከሞት ሊያድኑን እንደሚችሉ ስለታመነበት ነው። አንዳንድ መኪና አሽከርካሪዎች በየመንገዱ ዳር የሚያዩአቸውን የማስጠንቀቂያ ምልክቶችን ችላ በማለታቸው ምክንያት ለከፍተኛ አደጋ እንደተጋለጡ እናውቃለን። በምድር ለምናደርገው እንቅስቃሴ፥ ከአደጋ እንድናመልጥ ማስጠንቀቂያ ካስፈለገን፥ ለመንፈሳዊ ጉዞአችንማ ምን ያህል የበለጠ ያስፈልገን ይሆን? በመንፈሳዊ ጉዞአችን ላይ ከመስመር በቀላሉ ሊያወጡን የሚችሉ የሚታዩና የማይታዩ ልዩ ልዩ እንቅፋቶችና መሰናክሎች ያጋጥሙናል። አብዛኛዎቹ በሥጋዊ ዓይኖቻችን ማየት የማንችላቸው በመሆናቸው የግድ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች ያስፈልጉናል። መጽሐፍ ቅዱሳችን በእነዚህ የማስጠንቀቂያ ምልክቶች የተሞላ ነው። እ.አ.አ. በ1995 ዓ.ም. የመጽሀፍ ቅዱስ ጥናታችን ትኩረት የምንሰጠው ስለ እነዚህ ማስጠንቀቂያዎች ነው።*

*መጽሀፍ ቅዱስ ስለ ሰው ከሚናገራቸው እውነቶች መካከል አንደኛው "እግዚአብሔር ሰውን በራሱ መልክና አምሳያ ፈጠረው" (ዘፍጥረት 1፥27) የሚለው ነው። ይህ ጥቅስ አንዳንድ ሰዎችን ግራ ያጋባቸው ይመስለናል። "ሰው በእግዚአብሔር አምሳል ከተፈጠረ፥ እግዚአብሔር መሆን አለበት" በማለት ስለሚደመድሙ ነው። እግዚአብሔር ሰውን በአምሳሉ ሲፈጥረው፤ "እግዚአብሔር ወይንም አምላክ" አደረገው ማለት ሳይሆን፥ ቅዱስ እንዲሆን፣ ፈጣሪውን በትክክል እንዲያውቅ እያመሰገነውና እያከበረው ዘለዓለማዊ በሆነው ክብሩ ውስጥ እንዲኖር ፈጠረው ማለት ነው። ሰው ከምንጊዜውም የበለጠ ሰፊ ጊዜ ወስዶ ስለ ራሱ ከፍተኛ ጥናትና ምርምር ያደገበት ዘመን ቢኖር አሁን እኛ ያለንበት ዘመን ነው። የሥነ አዕምሮ ሊቃውንትና የሃይማኖት መሪዎች በአዲስ መልክ "እኛነታችን፣ ተፈጥሮአችንን" ለማሳወቅ በየጊዜው ቁጥር ስፍራ የሌላቸውን ጽሁፎችን እያዘጋጁ ያወጣሉ። አንዳንዶቻችን ይበልጥ ስለ ራሳችን ለማወቅ ከፍተኛ ጥማት ስላለን፥ ከእነዚህ መካከል ጥቂቶቹን አንብበናል። ዋናውና ትልቁ ምክንያታችን ሁላችንም "ራስ ወዳዶች" (egoist) በመሆናችን ይሆናል። ሰዎች በአልኮል መጠጥ መስከር እንደሚችሉ ሁሉ፥ በራሳቸው ፍቅር መስከር ይችላሉ። እነዚህኛዎቹ በአልኮል መጠጥ ከሚሰክሩት የሚለዩበት፥ በመጠጥ የሰከረ ሰው አልፎ አልፎ የሚያስቅ ቀልድ ወይንም ትዕይንት የሚታይበት ሲሆን በራሳቸው ፍቅር የሰከሩ ሰዎች ግን ለሚያዩአቸው ሁሉ የልብ ኃዘንና ስብራትን እንጂ ፈገግታን የማይሰጡ መሆናቸው ነው።*

### 1. ሰው ችግሩ ራሱን ማየት አለምቻሉ ነው

*ስለ ራሳችን የምናውቀው "አጉልቶ በሚያሳይ መነጽር" ተጠቅመን ያየነውን መልክና ቅርጽ ነው። ይሄ ራሳችን የፈጠርነው መነጽር፥ የሌለንን ቁመት ቀጣጥሎ የሌለንን ቁንጅናና ውበት አክሎ*

ስለሚያሳየን ይህን ያህል መጥፎ አይደለሁም” በማለት በግል ሕይወታችን ውስጥ መሻሻል ወይንም መለወጥ የሚገባውን ነገር እንዳናስተካክል ሆነናል። የሰው ችግሩ ራሱን በትክክል ማየት አለመቻሉ ብቻ ሳይሆን፥ ሌላው ቀርቶ “ለራሱም ቢሆን” እውነተኛ መሆን አለመቻሉ ነው። እኛ ራሳችንን ማየት ባንችልም፥ በቅርብ ሆነው ሕይወታችንን የሚያዩ በውስጣችን ምን ያህል በራስ ፍቅር መያዛችንን ሊጠቁሙን ይችላሉ። በማወቅም ሆነ ባለማወቅ ትክክለኛው “ማንነታችን” ለእኛል ሊታየን ባይችልም፥ ለሌሎች ግን በግልጽ ይታያል። የአሜሪካ ፕሬዚደንት የነበሩት ቲዮዶር ሩዝቬልት አንዳንድ ጊዜ “ሩዝቬልት አንደኛው” በሚል የቅጽል ስም ይጠሩ ነበር። እኚህ ሰው በራሳቸው ፍቅር የሰከሩ ነበሩ። በየትኛውም ጊዜ፥ በማንኛውም ሥፍራ የሰዎች ሁሉ ዓይን እሳቸው ላይ ብቻ እንዲያርፍ የሚፈልጉ ሰው ነበሩ። ከልጆቻቸው መካከል ይህንኑ ባህሪያቸውን የተገነዘበው አንደኛው ልጃቸው ስለ አባቱ ስለ ፕሬዚዳንት ሩዝቬልት ሲናገር፥ “አባባ ሁልጊዜ ሰው ሁሉ ወደ እርሱ እንደሚለከት፥ በማንኛውም ሥፍራ ራሱን ዋና (central) ማድረግ ይወዳል። ስለሆነም ሠርግ ቤት ስንሄድ ሙሽሪቷን መሆን ያምረዋል፤ ሰው ሞቶ ቀብር ስንሄድ ደግሞ የሞተውን ሰው (ሬሳውን) መሆን ባለመቻሉ ያዝናል” አለ።

## 2. ሰው ራሱን የሚወድበት ተፈጥሮአዊ ሕግ አለ

ሰው በተፈጥሮው ራሱን ይወዳል። ስለሆነም ሲርበው ያበላዋል፣ እንዳይቆሽሽ ያጥበዋል፣ እንዳይደነቁር ያስተምረዋል፣ እንዳይደክም ያሳርፈዋል፣ እንዳይሰለቸው ያዝናናዋል። ተስፋ እንዳይቆርጥ ያደፋፍረዋል። ራሱን ሳይበላ ማንንም አያበላም፣ ራሱ ሳይለብስን ማንንም አያለብስም፣ ራሱን ሳይጠቅም ማንንም አይጠቅምም። ራሱን የሚጠላ ሰው በአዕምሮው የታመመ ሰው ብቻ ነው። ራስን መውደድ ኃጢአት አይደለም። መጽሐፍ ቅዱስም ሰው ራሱን መውደድ እንዳለበት በቀጥታም ባይሆን በሌላ መልክ ሲገልጸው እናያለን። “ሰውን ሁሉ እንደራስህ አድርገህ ወደድ” (ማቴ. 22፥29) የሚለው የእግዚአብሔር ሕግ ሰው ራሱን መውደድ እንዳለብት ይጠቁማል። ሰው ራሱን መውደድ ባይኖርበት፥ ሌላውን የሚወድበት መጠን መመዘኛ ወይንም መለኪያ አይኖረውም ነበር። መጥፎ የሚሆነው ሰው ራሱን ብቻ ከመጠን በላይ የወደደ እንደሆን ነው።

## 3. መጠኑ ይለያይ እንጂ ሁላችንም “በራሳችን ፍቅር” እንያዛለን

ራስን መውደድ ኃጢአት ባይሆንም፥ ከመጠን ያለፈ የራስ ፍቅር ግን መንፈሳዊ ሕይወታችንን የሚበላ ነቀዝ ነው። በማወቅም ሆነ ባለማወቅ አልፎ አልፎ በራሳችን ፍቅር እንሰክራለን። ከማኛውም ዓይነት መነፈሳዊ ነቀዝ ይልቅ ይበልጥ ልንፈራውና ልንጠነቀቅ የሚገባው ይሄኛው ነው። በራሳችን ፍቅር ስካር ውስጥ ስንሆን፥ ብዙ ጊዜ ራሳችንን ማወቅ አንችልም። መንፈሳዊ ጥያቄያችንና ትኩረታችን እንኳ የሚያተኩሩት በራሳችን ላይ ብቻ ነው። አንዱ ሲጸልይ “ጌታ ሆይ! እባክህ በመንፈስ ቅዱስ ሙላኝ…ሙላኝ” እያለ ሲጮህ በራሱ ፍቅር የሰከረ መሆኑን በቅርብ የምታወቀው ሚስቱ “ጌታ ሆይ! አትሙላው፤ ብትሞላውም ቀዳዳ ነውና ያፈሳል” አለች። በራሱ ፍቅር የሰከረ ሰው ቋንቋውና ንግግሩ መነፈሳዊነት ይኑረው እንጂ ሕይወቱ ቀዳዳ ነው። በራስ ፍቅር መያዝ ምን ያህል አደገኛ መሆኑን የተረዳው ማርቲን ሉተር “ከጳጳሱ ይልቅ በጣም የምፈራው ራሴን ነው” ሲል ብዙዎች ደግሞ ያለማቋረጣ “ጌታ ሆይ እባክህን ከራሴ አስጥለኝ” እያሉ ሲጸዩ ይሰማሉ። ይሄ በመሠረቱ የሁላችንም ጸሎት ሊሆን ይገባል።

በማንኛውም ሰው ልብ ውስጥ “ዙፋን” ይኖራል። ዙፋን ካለ ደግሞ መስቀልም መኖር አለበት። ይህንን የተረዳው ኤስ. ዲ. ጎርደን የተባለው ጸሐፊ “በማኛውም ሰው ልብ ውስጥ ዙፋንና እንዲሁም መስቀል አለ። እነዚህ ሁለት ነገሮች አንድ ሰው ሳይቀመጥባቸው ባዶ የሚሆኑበት ጊዜ አይኖርም። የሰው ፈቃድ ሲያይል፥ በዙፋኑ ላይ የሚቀመጠው “ሰው” ነው፤ ዙፋኑን ሰው ከያዘው ደግሞ መስቀሉ ላይ የሚሆነው ኢየሱስ ነው” አለ። በልቡ ዙፋን ላይ እግዚአብሔር የተቀመጠ ከሆነ፥ ያ ሰው በእግዚአብሔር አገዛዝ ሥር ራሱን ያዋለ ሰው ነው። ሰው የመምረጥ ነጻነት ስላለው በዚያ ዙፋን ላይ ማን መቀመጥ እንዳለበት ወሳኙ ሰው ራሱ ነው። እግዚአብሔር በልቡ ዙፋን ላይ እንዲቀመጥ ከወሰነ፥ የሰው ራስ ወዳድነት ይጠፋና ትክክለኛውን ሥፍራ ይይዛል። በልቡ ዙፋን ላይ ሰው ራሱን የሚያስቀምጥ ከሆነ

ግን “ራሱን ያነገሰ ራስ ወዳድ” (egoist) ከመሆኑም በላይ እግዚአብሔርን ከሕይወቱ ያስወጣ ሰው ይሆናል።

## 4. የተሸፈነ “ራስ ወዳድነት”

ብዙዎቻችን “ራስ ወዳድ” መሆናችንን የመሸፈን ችሎታና ብልሃት አለን። በጥንቃቄ ላልተመለከተን ሰው ብዙ እናሳስልታለን። ጥሩ ምሳሌ የሚሆነን ሐዋርያው ጴጥሮስ ነው። የመንፈስ ቅዱስን ኃይል ከመቀበሉ በፊት በሕይወቱ “የራስ ወዳድነት” መንፈሱ ራሱን ከሌሎች ደቀ መዛሙርት ለየት አድርጎ በማቅረብ በግልጽ ይታይበት ነበር። ከጴጥሮስ ልምምዶች ውስጥ አንዱን ብቻ እንመልከት። ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን እግር ተራ በተራ ሲያጥብ ጴጥሮስ የሚታጠብበት ተረ ሲደርስ “ጌታ ሆይ! አንተ የእኔን እግር ከቶ አታጥበኝም” አለው (የዮሐ. 13፥8)። ይሄ እምቢታው የሚያሳየው “ሌሎቹ ደቀ መዛሙርት ጌታቸው እግራቸውን ሲያጥብ ዝም ማለታቸው ትክክል አይደሉም፤ እኔ ግን ከእነርሱ የተለየሁ ነኝ፤ ጌታዬ እግሬን እንዲያጥበኝ አልፈቅድም” ያለ ያስመስለዋል። ይህን ሲያደርግ በኢየሱስ ፊት ራሱን ከፍ አድርጎ ለማሳየት የተጠቀመበት ይሆናል ብለን እንገምታለን። ውስጡን ማየት የሚችለው ኢየሱስ ዋና ምክንያቱን ስላወቀ “እኔ እግርህን ካላጠብሁህ ከእኔ ጋር አንድነት አይኖርህም” አለው (የዮሐ. 13፥8)። ጴጥሮስ የመጀመሪያው ዕድል ሲያመልጠው፥ ሌላ ራሱን ከሌሎች የተለየ መሆኑን የሚያሳይበት ዘዴ ፈጠረ። “እንዲህስ ከሆነ እግሬን ብቻ ሳይሆን እጄንም ራሴንም እጠበኝ” አለው (የዮሐ. 13፥9)። ሌሎች ደቀ መዛሙርት በእግራቸው መታጠብ ሲበቃቸው፥ ጴጥሮስ ራሱን አሁንም ከሌሎች የተሻለ መሆኑን ለማሳየት የተጠቀመበት ይመስላል። ቢሆንም ኢየሱስ ሀሳቡን አልተቀበለውም (የዮሐ. 13፥10)።

አንዳንድ ሰዎች “ራሳቸውን ያላነገሱ” ትሁት ለመምሰል የሚጠቀሙበት ቋንቋ አላቸው። “…እኔ የማልረባ ነኝ፤…ወዳቂ ፋንድያ ነኝ! ፍጹም ዋጋ የሌለኝ፥…ከሰው ሁሉ የማንስ ፍጥሩ ነኝ” ይላሉ። ይህን ይበሉ እንጂ ብዙ ሳይቆዩ እውነተኛው ማንነታቸው ይገለጻል። በራስ ወዳድነት መንፈስ የተሞሉ ሰዎች ትምክህተኛነታቸውን የሚያሳዩበት መንገድ አላቸው።

ለምሳሌ፡-

- “የሚያስፈልገኝ ራስን የመግዛት ኃይል ነው፤ ከወሰንኩ ወይንም ቆርጬ ከተነሳሁ ይህን ያን ማድረግ እችላለሁ፤ ምንም የሚያስቸግረኝ ነገር የለም።”
- ከዛሬ ጀምሮ ይህን አላደርግም፤ “ማንም ይህንን አድርግ” ብሎ አያስገድደኝም፤ ከእንግዲህ ወዲያ በጅ አልልም…” ይላሉ። ያም ሆነ ይህ እግዚአብሔር ውስጣችንን ያውቃል። “የምታደርገው ነገር ሁሉ ትክክል የሆነ ሊመስልህ ይችላል፥ ነገር ግን እግዚአብሔር የመነሻ አሳብህን ይመዝናል” ይላል (ምሳሌ 16፥2)።

## 5. በራሱ ፍቅር የሰከረ ሰው በምን ይለያል?

*ሀ. ራሱን ከሁሉ በላይ ያደርጋል*

*ሀ.1. ራሱን ከሁሉ በላይ የሚያደርግ ሰው ስሜታዊ ነው።*

ራሱን ከሁሉ በላይ የሚያደርግ ሰው ለሚወስደው እርምጃ ወሳኙ ስሜቱ ነው። ማንኛውም ሰው በሕይወቱ ላይ ባለው የግል ኃይልና ሥልጣን መደነቁ አይቀርም። “ከእርሱነቱ” ውስጥ “ስሜቱ” የበለጠ ኃይለኛ ሆነው የሚታዩት “ፍርሃትና” “ቁጣ” ናቸው። እነዚህ ሁለት ስሜቶች በህይወታችን ውስጥ የሚኖራቸው ኃይልና ሥልጣን፥ ከውጪ ሆነው የሚያዩን ሰዎችን ብቻ ሳይሆን እኛኑ ጭምር ያስደንቀናል። እነዚህ ሰሜቶች ከውስጣችን ሲፈልቁ፥ ከእኛ በላይ በሆነ ኃይል የተገፋን ይመስለናል። ለመቆጣጠርና መስመር ለማስያዝ ከእኛ አቅም በላይ የሆነ መስሎ ይሰማናል። ይሁን እንጂ የዚህ ኃይል አመንጪው ሰው ራሱ ነው። ራሳቸውን ያነገሡ ሰዎች (egoist) በሕይወታቸው ለመወሰዱት እርምጃ ሁሉ “ፈቃድ ሰጪ” ወይንም ወሳኙ “ስሜታቸው” ነው። በሥነ አዕምሮ ጥናት የተሠማሩ ምሁራንም “ለስሜት” ከፍተኛ ደርጃና ሥፍራ ሲሰጡት ይታያሉ። ሰው ከውስጡ የሚሰማውን ስሜት እንዲገልጽ

ከሁኔታዎች ጋር ስሜቱን እንዲያለማምድ ስለ ራሱ ጥሩ የሆነ ስሜት እንዲኖረው፥ ስሜቱ ደስ ያለውን እንዲያደርግ ያደፋፍራሉ። በራሳቸው ፍቅር የሰከሩ ሰዎች ለስሜታቸው ከፍተኛ ሥፍራ ስለሚሰጡት፥ እነርሱን ካልተሰማቸው ምንም ዓይነት እርምጃ አይወስዱም፤ እነርሱ ሲያደርጉት ደስ ካላቸው ሌላውን ቢጎዱ፥ ሌላውን ቅር ቢያሰኙ ፈጽሞ ግድ የላቸውም። “ከስሜቴ ውጪ ሌላ ነገር ማድረግ ግብዝነት ነው” ብለው ስለሚያምኑ ትክክልም ባይሆን ከስሜታቸው ውጪ ማደርግ አይፈልጉም።

ሀ.2. በአዕምሮ ችሎታ “ከሁሉ እበልጣለሁ” ይላል

በራሱ ፍቅር የሰከረ ሰው ለስሜቱ ከፍተኛ ሥፍራ እንደሚሰጥ ሁሉ ለአዕምሮ ችሎታውም ከፍተኛ ሥፍራን ይሰጠዋል። አንብቦ ብዙ መረጃዎችን (information) በማወቁ በአዕምሮ ችሎታው ከሁሉም በላይ የላቀ መስሎ ይሰማዋል። በዚህም ልዩ ኩራት የሚሰማው ከመሆኑም በላይ ሌሎችን ዝቅ አድርጎ ይመለከታል። ለእንዲህ ዓይነቱ የእግዚአብሔር ቃል ማስጠንቀቂያ ይሰጣል “ራሳችሁን ብልሆችና ጥበበኞች አድርጋችሁ ለምትቆጥሩ ወዮላችሁ” ይላል (ኢሳያስ 4፥21)።

ሀ. 3. በሁሉም ነገር “እኔ ልክ ነኝ” ይላል

ራሱን ያነገሰ ሰው ሁልጊዜ “እኔ ልክ ነኝ” ይላል። ይህንን አቋሙን ማንም ሊያስለውጠው አይችልም። መሳሳቱን አውቆ “ተሳስቻለሁ! ይቅርታ” ማለት አይሆንለትም። አለማወቁን ይደብቃል። አለማወቁን የሚሸፍንበት የራሱ መንገድና ብልሃት አለው። አለማወቁ ከታወቀበት ይበሳጫል። መታረም አይወድም። መጽሐፍ ቅዱስ “ትዕቢተኛን ሰው ብታርመው ስድብን ታተርፋለህ” ይላል (ምሳሌ 9፥7)።

ሀ.4. ራሱን ፍጹምና ጻድቅ አድርጎ ያያል

በራሱ ፍቅር የሰከረ ሰው በራሱ ቅድስና፣ በሌሎች ድካም ያምናል። ይሄ ካልሆነ ተራ ሰው የሆነ ይመስለዋል። “ተሳስቻለሁ” ማለቱ “ምንም ጥቅም የለውም” ብሎ ያምናል። ብርታቱ እንጂ ድክመቱ አይታየውም፤ ዕውቀቱ እንጂ ድንቁርናው አይገባውም። ራሱን ጻድቅ አድርጎ ስለሚያቀርብ በሕይወቱ ለሚደርሰው ማንኛውም ነገር ምክንያት ይሰጣል። ለምሳሌ ወደ ሥራው ሲሄድ መንገድ ላይ የመኪና ጎማው ቢፈነዳ፥ ጎማው ብዙ ስላገለገለ አርጅቶ ነው በማለት ፈንታ፥ “ለጌታ የቆምኩ ብርቱ ክርስትያን በመሆኔ ሰይጣን እኔን እየተዋገኝ ነው” ይላል። የልጁ ሠርግ ዕለት ዝናብ መዝነቡ ቀርቶ ጸሐይ ቢወጣ፥ እግዚአብሔር ይህን ያደረገው ለእርሱ ሲል ይመስል “ጌታ ቅንነቴን፣ ንጽሕናዬን አይቶ ጸሐይ ወጣልኝ” ይላል።

.....................................................................................

**በሚቀጥለው ክፍል እስክንገናኝ፥ የጌታ ጸጋና ሰላም ከሁላችን ጋር ይሁን።**